# የኬንያ አልሸባብ ፍጥጫ

(በዮሀንስ አልታሞ)

በአፍሪካ ቀንድ የተረጋጋች አገር ተምሳሌት ተብላ በምዕራባውያኑ ሚዲዎች የምትሞካሸዋ ኬንያ ከ .ኤ.አ 2007 አገራዊ ምርጫ ማግስት ጀምሮ መረጋጋት ርቋታል፡፡ ከሁለት ሺህ በላይ የሚጠጋ ህዝቢን ሰውቶ ያለፈው ምርጫ በኬንያ  ታሪክ ትልቅ ጠባሳ ጥሎ ያለፈ ብቻ ሳይሆን የኬንያን የፖለቲካ ሁኔታ ውስብስብነት አጋልጦም ያለፈ ክስተት ነበር፡፡ አገራችን ኢትዮጵያ በ1997 ያደረገችውን አገራዊ ምርጫ ተከትሎ የተከሰቱ ግጭቶች ለዜጎች ህልፈት ምክንያት ቢሆንም ከየትኛውም የፖለቲካ  እና ሚዲያ ወገን ቁጥሩም ሆነ የነበረው ውድመት ከኬንያ ድህረ ምርጫ ክስተት ጋር ፈፅሞ ሊስተካከል አይችልም፡፡ ይሁንና በምዕራባውያን ማዲያ  እና ሰባአዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች ከአመታት ላላነሰ ጊዜ ለበርካታ  ጊዜ በዋና ዜናነት  እና አጀንዳነት ተይዞ መቆየቱ ይታወሳል፡፡ ይህ የአለም አቀፍ ግኑኝነት ውግንና ባህሪ ገላጭ መሆኑ የማይታበል ሀቅ ቢሆንም ኬንያ የአብዛኛዎቹ አለም አቀፍ ሚዲያወች የምስራቅ አፍሪካ መቀመጫ መሆኗም ሳያግዛት  እንዳልቀረ ይነገራል፡፡ ይህም ሆኖ የኬንያን ውጫዊ ገጽ  ከመገንባት ያለፈ በውስጡ ላለው ችግር መፍትሄ ሊያመጣ አልቻለም፡፡ ኬንያ ልብ ለልብ በማይተዋወቁ ሁለት የፖለቲካ ጽንፍ  የተመራች ነው፡፡ በፕሬዘዳንቱ  እና በራይላ ኦዲንጋ የሚመራው ኦሬንጂ ዲሞክራቲክ ሙቭመንት አገሪቱን በጥምር  ያስተዳደሯት ይገኛሉ፡፡ ከአገራዊ ምርጫ ማግስት ጀምሮ  ምርጫውን የተሸነፈ  እና የአሸናፈ ስልጣን በድርድር ተከፋፍለው አገሪቱን በውጥረት  የመሯት ነው፡፡ የአንደኛው ውሳኔ ለሌኛ ው ግልፅ ማይሆንበት  እና በርካታ  አስተዳደራዊ ውዝግቦች  እንዳሉም ይነገራል፡፡ ሆኖም ይለየን ብለው ምርጫ 2012ን  የተጠባበቁ ነው፡፡ ህዝቡም ይህንኑ ተስፋ ያደርጋል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ ኬንያ አዲስ ውጥረት ውስጥ ገብ ለች ለመጪው ምርጫ ፓርቲዎቹ የቤት ስራቸውን በመስራት በሚገኙበት ወቅት የተከሰተው ክስተት ኬንያን ወደ ማያባራ ጦርነት ሊያስገባት ይችላል የሚሉ መላምቶች ከየአቅጣጫው የጎረፉ ናቸው:: ከኬንያ ዳዳብ የስደተኞች መጠለያ ጣቢያ የተወሰዱት ሁለት ስፔናውያን የዕርዳ ሠራተኞች መታገት እና ጢቂት ቀናት ቀደም ብሎ ከላሙ የሪዞርት ስፍራ ግተው የገቡበት ደብዛቸው የጠፋው ሁለት የእንግሊዝ እና የፈረንሳይ ዜግነት ያላቸው ቱሪስቶች ለኬንያ የፀጥታ ስጋት ከመሆን ባለፈ በአመት አምስት መቶ ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ በሚያስገኘው በቱሪዚም ኢንደስትሪ ላይ የተቃጣ ጥቃት መሆኑን ኬንያዎች በአፅኖት የተናገሩ ይገኛሉ:: መንግስትም አልሸባብን በጉዳዩ ላይ ቀጥተኛ ተጠያቂ ንደሆነ ይፋዊ መግለጫ አውጥቶ አልሸባብን በሶማሊያ ያደነ ነው:: ስከአሁንም ከአንድ መቶ ያላነሱ የአልሻባብ ተዋጊዎች መግደሉንና ቀደም ሲል በደቡብ ሶማሊያ የያዙትን ስፍራ ያስለቀቀ ለሽግግር መንግስቱ ያስረከበ መሆኑን የኬንያ ወታደራዊ አመራሮች የገለፁ ናቸው::

በእርግጥ ኬንያ የአሸባሪዎች ጥቃት ሰለባ ስትሆን የመጀመሪያ ጊዜዋ አይደለም፣ በፍሊስጤም ነፃ አውጭ ድርጅት በናይሮቢ በሚገኘው የአይሁዶች ሆቴል ላይ በተቃጣ ጥቃት አስራ አምስት ሰዎች ሞተዋል፣ ከአስር አመት በፊት በኬንያ የአሜሪካ ኤምባሲ ላይ አንድ ቶን የቲ.ኤን.ቲ ፍንዳታ ተከስቶ ከሁለት መቶ ሰዎች በላይ የጥቃቱ ሰለባ የሆኑ ሲሆን ማንነ ታቸው ያልታወቁ ግለሰቦች በሞንባሳ የእስራኤላውያን ሆቴል ላይ በከፈቱት ተኩስ አስራ አንድ ኬናውያንና ሶስት እስራኤላውያን ሞተዋል፣በሞይ አለም አቀፍ ኤርፖርት በእስራኤል አውሮፕላን ላይ የተተኮሱ ሁለት ሚሳኤሎች ኢላማቸውን ለጥቂት ስተዋል፣ እነዚህን ጥቃቶች ተከትሎ የኬንያ መንግስት ውስጣዊ ቁጥጥሮችን በወቅቱ ጠበቅ ያደረገ ቢሆንም «ሽብርተኝነትን ከምንጩ» በማለት ሶማሊያ የተጠለሉ አሸባሪዎችን ሲያሳድድ ወይንም የተለየ እርምጃ ሲወስድ አልተስተዋለም

ነበር፡፡ የአፍሪካ ቀንድ ለእርስ በእርስ ግጭቶች ተጋልጦ የቆየና ጠንካራ መንግስታትን ሳያፈራ የከረመ ክልል በመሆኑ የአካባቢውን ደካማ ጎን በመጠቀም የሽብር አላማቸውን ለማሳካት አሸባሪዎች መጠለያ ቤታቸው አድርገው መክረማቸው ገሃድ የወጣ ነው፡፡ በተለይም መንግስት አልባዋ ሱማሊያን ማኮብኮቢያ ጣቢያ በማድረግ ለሱማሊያና ጎረቤት አገራት የስጋት ምንጭ ሆነዋል፣ በዚህም የሽብር ጠበል ያልቀመሰ የጎሮቤት አገር አለ ለማለት አያስደፍርም፡፡ አገራችንም በሶማሊያ ስላማዊ ፍርድ ቤቶች ህብረት የተጋረጠባትን አደጋ ለመከላከል ወ ደሮችዋን ወደ ሶማሊያ መላኳና በወቅቱ ሀያል መስሎ ያስፈራራውን ሀይል አስወግዳ፣ የከፈለችውንም ዋጋ ከፍላ መመለሷ ይ ወቃል፡፡ በወቅቱ በሶማሊያ የሰፈሩ የአሸባሪዎች ስብስብ ላይ ከኢትዮጵያ ውጪ ብዙም ትኩረት የሰጠ የጎረቤት አገር ያለ አይመስልም ነበር፡፡ እንዲያውም አንዳንዶች ሉአላዊቲ ሶማሊያን እንደደፈረሰች አድርገው ጥርጣሬ ውስጥ የገቡበት ሁኔታ ተስተውሎአል፡፡ ውነታው እያደር ይገባል እንዲሉ በሂደት ኡጋንዳም የጥቃቱ ሰለባ ሆነች፡፡ ከአንድ አመት በፊት በካምፓላ የኳስ ጨዋታን በቴሌቭዥን በሚከታተሉ ንፁሀን ዜጎች ላይ የደረሰው ጥቃት በቀጥታ ሶማሊያ በመሸገው አልሸባብ የተፈጸመ መሆኑን አልሸባብ ራሱ ሀላፊነት በመውሰድ አረጋግጧል፡፡ ይሁንና አገራት ለአጸፋው የሰጡት ምላሽ ምንም የሚባል ነው፡፡ ኬንያም የሶማሊያን የሽግግር መንግስት ለማቋቋም የተደረጉ ድርድሮች ላይ በርካታ ስብሰባዎችን በአገሩዋ ከማስተናገዱ እና ድጋፍ ከማድረጓ ባሻገር በአሸባሪዎች ከደረሰባት ጥቃት አንጻር የከረረ ርምጃ በመውሰድ ተቀዳሚውን ስፍራ ስትይዝ አይስተወልም፡፡ የኤርትራ መንግስት ሽብርተኝነትን ከማውገዝ እና ከመዋጋት ይልቅ አሸባሪዎችን በአገሩ በማስጠለል እና አስፈላጊውን ድጋፍ በማድረግ አልፎ አልፎም አሸባሪዎቹ የነፃነት ታጋይ ናቸው በማለት ጥብቅና በመቆም ከአሸባሪዎች ጋር ያለውን ጥብቅ ግንኙነት አመላክቷል፡፡አልሸባብንም ሆነ ሌሎች አሸባሪ ድርጂቶችን ሲያወግዝ የማይስተዋለውም ከዚህ ቅርርቡ የተነሳ ነው፡፡

በቅርቡ የ.ተ.መ.ድ ሞኒተሪንግ ቡድንም ያቀረበው ሪፖርት ይህንኑ አረጋግጧል፡፡

ሱዳንም ከሽብርተኞች ጋር ያላት ንኪኪ ሙሉ በሙሉ ግልፅ ያልሆነ ብሎ ከማስቀመጥ ያለፈ ለአመታት የኦሳማ ቢንላደን መጠለያ ስለነበረችው ሱዳን ብዙ ማውራት ጊዜ ማጥፋት ይሆናል፡፡ሁሉም ግልጥልጥ ያለ በመሆኑ ፣በመሆኑም የአፍሪካ ቀንድ አገሮች የሽብርተኝነት ተጠቂ እና ደጋፊ ብሎ ማስቀመጡ የተጋነነ ውነት ሊያስብል አይችልም፡፡ ሆኖም አገራቱ ሽብርተኝነትን በመዋጋት ዙሪያ አንድ አይነት አቋም ይዘው ከመዋጋት ይልቅ በተናጠል የሚያደርጉት ሩጫ ወቃሽና ተወቃሽ ያበዛ የመጣ ከመሆን በተጨማሪ በጎሮቤት አገሮች አለመተማመን ንዲነግስ በር ሲከፍት ይስተዋላል፡፡ በርግጥ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በኢጋድ ማዕቀፍ የሚደረጉ ምክክሮች ከዚህ አንፃር በአወንታ መልኩ የሚጠቀሱ መሆናቸው አበረታች መሆኑ የማይታበል ሀቅ ነው፡፡

ይህም ሆኖ ኬንያ ወደ ሶማሊያ የገባችበትን አካሄድ ሁሉም የጎረቤት አገሮች በምን አይነት እይታ ተመለከቱት የሚለው ግልፅ ባይሆንም ከአለም አቀፍ ማህበረሰብ እና በውጭ ባሉ የሶማሊያ ዲፕሎማቶች የተለያዩ አስተያየቶች ስሰነዘሩ ሰነባብተዋል፡፡ ኬንያ ወደ ሶማሊያ የገባችበት ሁኔታ ከሽግግር መንግስቱ ባለስልጣናት ጋር ምክክር ያልተደረገበት እና የአገሪቱን ሉአላዊነት የተጋፋ ነው የሚለው አስተያየት የኬኒያ ወታደሮ ወደ ሲማሊያ ድንበር ከገቡበት ከመጀመሪያው ቀን ጀምሮ ጎላ ብሎ የሚደመጥ ነበር፡፡ ይሄንን ሁኔታ በቸልታ ያላየው የኬንያ መንግስትም የውጭ ጉዳዩን እና ሌሎች ከፍተኛ ባለስልጣናትን ወደ ሞቃዲሾ ልኮ ከሽግግር መንግስቱ ባለስልጣናት ጋር ድርድር በማድረግ ስምምነት ላይ መድረሱን ተናግሮአል፣ ወደ ሶማሊያ የገባበትንም ሁኔታ በሚመለከት በአገር ውስጥ ደህንነት አማክኝነት መግለጫ ሰጥቷል፣ በዚህም በተ.መ.ድ ቻርተር በአስራ አምስተኛው አንቀፅ አገሮች ራሳቸውን ከወረራ ንዲከላከሉ

የሚፈቅደውን ስምምነት መሰረት በማድረግ የሚካሄድ ኦፕሬሽን መሆኑን ገልፆአል:: ይህን መግለጫ ተከትሎም የአየር ሃይል እና ታንኮች አልሻባብን ለማዳከም እና ታጋቾችን በማፈላለግ ስራ ተጠምዶዋል:: ኬኒያውያን ከሽግግር መንግስቱ ከፍተኛ ባለስልጣናት ጋር ተነጋገርን ይበሉ እንጂ ፕሬዝደንት ሽሪፍ ሼክ አህመድ ኬኒያ ተስማምተናል ስላለቸው ስምምነት ሲገልጹ ኬኒያዎች የሶማሊያን ወታደር እንዲያሰለጥኑና ሌሎች ድጋፎች እንዲያደርጉ እንጂ ወደ ሲማሊያ ጦራችውን ንዲያስገቡ አለመሆኑን ተናግረዋል:: የሶማሊያው ጠቅላይ ሚኒስትር አብዲወሊም ቢሆኑ ኬኒያወች በሚሉት መልኩ ያደረጉት ስምምነት እንደሌለ የተናገሩ ሲሆን አንዳንድ የሽግግር መንግስቱ የፓርላማ አባላትም ኬኒያ በሶማሊያ ለተሰማራው ለአፍሪካ ህብረት ሰላም አስከባሪ ሀይል ጦሩዋን ለማዋጣት ፍቃደኛ ያልሆነች አገር ሶማሊያ ውስጥ ምን ትሰራለች ብለው ይጠይቃሉ::ይሁንና ከቅርብ ጊዜ ወድህ ለዘብተኛ አቋም በማሳየቱ ከሽግግር መንግስቱ ጋር ግንባር ፈጥሮ አልሸባብን በመውጋት ላይ የሚገኘው የአሁሉ ሱና ዋል ጃማ ቃልአቀባይ ሼክ ሞሀመድ ሁሴን የኬኒያን ወደ ሶማሊያ መግባት በመደገፍ ይህን የተቃወመውን ፕሬዚደንቱን ደግሞ ከአልሸባብ ጋር ካለው የቀድሞ ወዳጂነት የመነጨ እና አልሸባብ ፈጽሞ እንዲወገድ ፍላጎቻቸው መሆኑ ላይ ጥርጣሬ እንዳላቸው ገልጸዋል:: በመግለጫቸውም የኬኒያ መግባት ለአልሸባብ መዳከምና መወገድ ወሳኝ በመሆኑ ስከዚያው ድረስ የኬኒያ ወታደሮች ከሶማሊያ እንዳይወጡ ጠይቀዋል:: እንግዲ ኬኒያ ድንበሮዋንና ህዝቢን ከጥቃት ለመታደግ ወደ ሶማሊያ የመግባቷ ጉዳይ በትልቅ ውጥረት የታጀበ እንደሆነ ማይት ይቻላል:: ኬንያ በሱማሊያ ስለሚኖራት የጊዜ ገደብ ምንም የተገለፀ ነገር የለም:: ከአልሸባብ ጋር የተያያዘችውን ጦርነት በምን መልኩ ትደመድመዋለች? ኢትዮጵያ የ ስላማዊ ፍርድ ቤቶች ስብሰባን መሰረት ከሶማሊያ አጥፍ ንደወጣች አለም አቀፍ አሸባሪ ከሆነው አሸባሪ ድርጅት አልቃይዳ ጋር ቀጥተኛ ግንኙ -ነት ያለውን አልሻባብን በአጭር ጊዜ የማውደም ወ ደራዊ ጥንካሬ እና የሎጀስቲክ አቅርቦት ዝግጅት ኬንያ አላት ወይ? አሜሪካ በፖኪስታንና

አፍጋንሲታን አልቃይዳን ለማዳን የዘረጋችው ስትራቴጂ አሜሪካንና ህዝቧን የሽብርተኝነት ኢላማ አድርጓቸዋል፣ ጦርነቱም ማብቂያ የሌለው ሆኖአል በመሆኑም ኬንያ በተናጠል ከአልሸባብ ጋር የም ደርገው ጦርነት የኬንያን የወደፊት ጣ ፈን ከምን ሊያደርስ ንደሚችል መገመት ቀላል የማይሆንበት ሁኔ ተፈጥሮአል:: የሶማሊያ ሪፓርት ድህረ ገጽ እንደዘገበው ይህንንም ፍራቻ ይመስላል የኬኒያን ረዳት የውጪ ጉዳይ ሚንስትር ሪቻርድ ኦኞክን ጨምሮ አንዳንድ ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናት የሁለት ሺ ስምንቱን የጂቡቲውንና የቅርቡን የካምፓላ ስምምነት በማይጎዳ መልኩ ከአልሸባብ ጋር ድርድር ለማድረግ ዝግጁ መሆናቸውን የሚገልጽ መግለጫ የሰጡ የሚገኙት::

ዋነኛ የኢኮኖሚ መሰረቷ የቱርዝም ኢንድስትሪ መነካት ለኬኒያ ምን ያህል ጉዳት እንደሆነ የወሰደች ያለውችው እርምጃ አመላካች ነው:: ኬንያና ቱርዝም የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽ ሆነዋል ::ጦርነቱ የሰላም እና የደህንነት ብቻ ሳይሆን የኢኮኖሚም ነው፣ ከዚህ ቀድሞ በኬንያ ተቃጥቶ በነበሩ የሽብር ጥቃቶች መነሻነት አሜሪካን ጨምሮ ሌሎች የአውሮፓ አገራት ዜጎቻቸው ወደ ኬንያ የሚያደርጉት ጉዞ ላይ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ የማስጠንቀቂያ ምክር አውጥተዋል:: በዚህም በኬንያ የቱሪስት ፍሰት በእጅጉ በመቀነሱ ኬንያ ከፍተኛ ገቢዋን አጥ ለች:: ይህ አይነቱ ሁኔ ንዳይከሰት አሁንም አገሪቱ ከፍተኛ ፍርሃት ውስጥ ያለችበት ወቅት ነው:: ለዚህም ይመስላል ያልጠበቀችውንና ያልተዘጋጀችበትን መስዋዕትነት ለመክፈል ወደ ሶማሊያ የገባቸው:: የኬንያ ወታደሮች በአስቸኳይ ከሎአላዊት አገር ሶማሊያ ካልወጡ ሁሉን አቀፍ የሆነ እርምጃ በኬንያ ላይ ሊወስዱ እንደተዘጋጁ አልሸባቦች በቃል አቀባያቸው አማካኝነት ዝቷል፣ ከዛቻው ወዲህም በኬኒያ ዋና ከተማ አንዳንድ ፍንዳታወች ተስተውለዋል በኬኒያ ዜጎች ላይም ጉዳት ደርሲል:: በርግጥም የአልሸባብ ዛቻ ተግባራዊ የሚሆን ከሆነ የኬንያ ሽብርተኝነትን የመከላከል ልምድና ዝግጅት ለፍተሻ ይጋለጣል:: በአጠቃላይ የፀረ ሽብር ዘመቻው የዚህኛው ወይንም የዛኛው አለመሆኑ ለኬንያም ግልፅ የሚሆንበት ወቅት አሁን ነው፣ ኢትዮጵያ

በሽብርተኝነት መዝግቧ ካሰፈረቻቸው መካከል ኦነግ  እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በኬንያ ውስጥ  እንደነበር የሚታወስ ነው። የአፍሪካ ቀንድ የፀረ ሽብር ግንባር ፈጥሮ መንቀሳቀስ አስፈላጊ መሆኑን ቆይቶም ቢሆን አገራት መረዳታቸው  እንደማይቀር ኬንያ አንዷ ማሳያ ሆናለች። ሰላም!